Paid Leave Oregon

# ለጥቅማጥቅሞችለማመልከትምንእንደሚያስፈልግዎ: የህክምና እረፍት

ለጥቅማጥቅሞችለማመልከትለመዘጋጀትየሚያግዝዎትንይህንንዝርዝርይጠቀሙ።

## ሽፋን ለማግኘት የመሰረጡ ሰራተኞች እና የራሳቸውን ስራ የሚሰሩ ሰዎች የሚከተለውን ማድረግ ይችላሉ፡

- የFrances Online መለያ/አካውንት ይፍጠሩ
- በFrances Online መለያቸውበኩልበአንላይንለጥቅማጥቅሞችማመልከት
- ለጥቅማ ጥቅሞች በመልዕክት ወይም በስልክ ማመልከት:
  - የማመልከቻ ቅጹን ከ የሚከፈልበት እረፍት ድረገጽ ላይ ማውረድ እና ፕሪንት ማድረግ
  - 833-854-0166 (ከክፍያ ነጻ) ለእኛ መደወል

Frances Online ለሚከፈልበት እረፍት ለማመልከት **ፈጣኑ እና ቀላሉ መንገድ** ነው። Frances Onlineን ማግኘት ካልቻሉ የወረቀት ማመልከቻ ይላኩልን ወይም በስልክ ለማመልከት ይደውሉ። የሚያመለክቱት በወረቀት ወይም በስልክ ከሆነ ምላሽ ለማግኘት ረጅም ጊዜ ሊወስድብዎ ይችላል።

እርስዎን ወክሎ የተመደበ ተወካይ ቅጽን በመሙላት ለሚከፈልበት እረፍት ጥቅማ ጥቅሞች የሚያመለክትልዎ ሰው ሊኖርዎት ይችላል። እባክዎ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሰራተኛ መመሪያን ይመልከቱ።

በኦሬጎን የሚከፈልበት እረፍት/ Paid Leave Oregon / ላይ ከመሳተፍ ይልቅ አሰሪዎ ተመጣጣኝ ዕቅድ ካለው በዛ ተመጣጣኝ ዕቅድ ስር የተለየ ማመልከቻ ማስገባት አለብዎ። ይህንእንዴትማድረግእንዳለብዎትመመሪያዎችእንዲሰጥዎአሰ ሪዎንይጠይቁ።

## ይዘጋጁ

**ከማመልከትዎበፊት፡-**

- ☐ ለአሰሪዎያሳውቁ — የእረፍትጊዜዎከመጀመሩ 30 ቀናትበፊትለአሰሪዎመንገርአለብዎት። ለድንገተኛ ሁኔታ የ24 ሰዓት የቃል ማስታወቂያ ሊሰጧቸው እና ከዚያም በ3 ቀናት ውስጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ እስኪደርስዎ ሊከታተሉ ይችላሉ። ማስታወቂያ መስጠት ካልቻሉ ሌላ ሰው ይህን ሊያደርግልዎ ይችላል።

  **ማስታወሻ፡-** ለአሰሪዎ ስለ እረፍትዎ በተመለከተ ማስታወቂያ መስጠትዎን ማሳየት ካልቻሉ የሚከፈልበት እረፍት የመጀመሪያውን ሙሉ ሳምንታዊ የጥቅማ ጥቅም ክፍያዎች በ25% ሊቀነስ ይችላል።
- ☐ የሚፈልጉትንመረጃ - የእያንዳንዱእርምጃዝርዝሮችእንድላይተሰብስበውበዚህዝርዝርውስጥተካትተዋል።
- ☐ የFrances Online የጠያቂ መለያ/አካውንት ይፍጠሩ — Frances Online ለጥቅማ ጥቅሞች ለማመልከት ፈጣኑ መንገድ ነው። የሚሰሩት የራስዎን ስራ ከሆነ ይህ የጠያቂ መለያ/አካውንት ሁለተኛ መለያ/አካውንት ነው። ይህ ሽፋን ለማግኘት ለማመልከት ከፈጠሩት የአሰሪዎ መለያ/አካውንት ጋር አንድ አይነት አይደለም።

## እርምጃ 1፡- የFrances Online አካውንትይፍጠሩ

**መለያለመፍጠርየሚያስፈልግዎነገር፡-**

- ☐ ሙሉህጋዊስምዎእናየትውልድቀንዎ።
- ☐ የማህበራዊዋስትናቁጥርዎ (SSN) ወይምየግልየግብርከፋይመለያቁጥርዎ (ITIN)።

- ☐ ስልክቁጥርዎን፣ የኢሜይል አድራሻዎን፣ አካላዊ አድራሻዎን እና ከአካላዊ አድራሻዎ የተለየ ከሆነ፣ የመልዕክት አድራሻዎን ጨምሮ የግንኙነት መረጃዎ።
- ☐ የስቴትዎመንጃፍቃድወይምየስቴትመታወቂያካርድ (ካለዎት)።
- ☐ የኢሜይል አድራሻዎ።
- ☐ ቀደም ሲል ለሚከፈልበት እረፍት ወይም የስራ አጥነት መድን/Unemployment insurance ዕቅድ ጥያቄ አስመዝግበው ከሆነ መለያዎን/አካውንትዎን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስተካከል ደብዳቤ እንድንልክልዎ እኛ ልናስፈልግዎት እንችላለን።

## እርምጃ 2፡- ለጥቅማጥቅሞችያመልክቱ

**በፍራንሲስኦንላይንላይመለያከፈጠሩበኋላወዲያውኑማመልከትይችላሉ። ለማመልከት ለFrances Online ይመዝገቡ። በተጨማሪም የጥቅማ ጥቅሞች ማመልከቻ ከድረገጻችን ላይ ማውረድ እና ለእኛ በመልእክት መላክ ወይም በስልክ ለማመልከት በስልክ ቁጥር 833-854-0166 መደወል ይችላሉ።**

### ለማመልከትምንእንደሚያስፈልግዎ፡-

- ☐ በFrances Online በኩል የሚያመለክቱ ከሆነ የተጠቃሚ ስምዎ እና የይለፍ ቃልዎ።
- ☐ የማህበራዊዋስትናቁጥርዎ (SSN) ወይምየግልየግብርከፋይመለያቁጥርዎ (ITIN)።
- ☐ የሚያመለክቱበት እረፍት አይነት።
- ☐ የጠየቁትየዕረፍትመርሃግብር (ተከታታይኢሊያምጊዜያዊ) እናየሚከፈልበትየእረፍትጊዜየሚጠበቁትየመጀመሪያእናየመጨረሻቀናት።
    - ተከታታይእረፍትማለትእረፍትዎከሚጀምርበትቀንእስከሚያበቃበትቀንድረስበመካከሉባለውጊዜውስጥምን ምአይነትስራሳይሰሩእረፍትዎንሲወስዱነው።
    - የተቆራረጠ እረፍት ማለት በእረፍትዎ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ቀናት መካከል የቀናት ወይም ሳምንታት እረፍት ሲወስዱ ነገር ግን በእረፍትዎ ላይ እያሉም ሲሰሩ ነው። ለሁለት ወይም ከዚያ ባላይ የኑሮ ሁኔታዎች በተመሳሳይ ጊዜ እረፍት የሚወስዱ ከሆነ የተቆራረጠ እረፍት መውሰድ አለብዎ።
- ☐ የአሁኑእናያለፉት 18 ወራትየስራመረጃዎየሚከተሉትንጨምሮ፡-
    - የአሰሪ የንግድ ድርጅት ስም፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር
    - የአሰሪዎ የንግድ ድርጅት መለያ ቁጥር (BIN) ወይም የፌደራል አሰሪ መለያ ቁጥር (FEIN) (እነዚህን ቁጥሮች ከአሰሪዎ ይጠይቁ)
    - የስራመደብዎመጠሪያ (ስራዎትንለማግኘትእንዲረዳዎ)
    - የተቀጠሩበትቀን
    - በአሰሪዎ በየ ምን ያክል ጊዜ ይከፈልዎታል
    - አሰሪዎ ምን ያክል ይከፍልዎታል
    - አብዛኛውንጊዜለእያንዳንዱአሰሪየሚሰሩትበየሳምንቱየቀናትብዛት
    - ስለእረፍትዎለአሰሪዎየነገሩበትቀን
- ☐ ሊያገኙት የሚችሉት የሰራተኞች የክፍያ ጊዜ ክፍያ ማጣት ጥቅማ ጥቅሞች ወይም የስራ አጥነት መድን/Unemployment insurance ፕሮግራም ጥቅማ ጥቅሞችን የተመለከተ መረጃ።

- ☐ ስላሉዎትማንኛውምተመጣጣኝየእቅድሽፋንእናበዚህዕቅድስርስለወሰዱትየትኛውምከክፍያጋርየሚሰጥእረፍትየተመለከተመረጃ።
- ☐ ጥቅማጥቅምዎየሚከፈልበትየሚመርጡበትዘዴ። በቅድሚያከተከፈለየዴቢትካርድእናቀጥተኛተቀማጭመካከልመምረጥይችላሉ። ቀጥተኛተቀማጭገንዘብከመረጡ፣የባንክሒሳብዎንእናየማስተላለፊያቁጥሮችያስፈልግዎታል።
- ☐ የግብርተቀናሽምርጫዎ።

## እርምጃ 3:- የማንነት ማረጋገጫ

ማመልከቻዎ ከደረሰን በኋላ ማንነትዎን እናረጋግጣለን። አንዳንድ ጊዜያት ማንነትዎን ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃ ልንፈልግ እንችላለን። መለያዎን/አካውንትዎ በሚከፍቱበት ወቅት የኢሜይል ማስታወቂያዎች ለማግኘት መርጠው ቢሆንም እንኳ በዩ.ኤስ መልዕክት ደብዳቤ እንልክልዎታለን። **እባክዎ የዩ.ኤስ መልዕክትን ይመልከቱ** እና ሊኖሩን ለሚችሉ ለየትኛውም የክትትል ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ዝግጁ ይሁኑ።

## እርምጃ 4:- የአኗኗር ሁኔታዎን ማረጋገጥ

**የህይወትክስተትዎንለማረጋገጥየሚያስፈልግዎነገር**

በFrances Online መለያዎ/አካውንትዎ ላይ ስለ ጥያቄዎ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ የሚጠይቅዎ መጠይቅ ይኖራል። ወደ Frances Online መለያዎ/አካውንትዎ መግባት እና መጠይቁን ማጠናቀቅ ይኖርብዎታል። በተጨማሪም ብቁ የሚያደርግ የአኗኗር ሁኔታዎን ለማረጋገጥ ሰነዶችዎን (ከታች ተዘርዝረዋል) እንዲልኩልን እንጠይቅዎታለን። ይህን ለማድረግ ቀላሉ መንገድ ለጠያቂዎች መለያ/አካውንት ይህን በFrances Online easiest ላይ ካለው መልዕክት ጋር አብሮ መላክ ነው። የFrances Online መለያ/አካውንት ከሌለዎ የማረጋገጫ ሰነዶችዎን ከወረቀት ማመልከቻዎ ጋር በመልዕክት ይልኩልናል። በተጨማሪም ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ልንደውልልዎ እችላለሁ።

የምንጠይቃቸው የማረጋገጫ ሰነዶች እርስዎ እንደሚፈልጉት የእረፍት አይነት ላይ ይመሰረታል። ከታች ከተዘረዘሩት ሰነዶች ውስጥ አንዱን ሰነድ ለእኛ መስጠት አለብዎ። ይህ ሰነድ እረፍትዎን ለማረጋገጥ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች የማያካትት ከሆነ ተጨማሪ መረጃ ልንጠይቅዎ እንችላለን።

በዚህ ዝርዝር ላይ የተገለጹት ሰነዶች በጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል የጤና እንክብካቤ አቅራቢ መሞላት ያለባቸው ክፍሎች ሊኖሯቸው ይችላሉ። ከሚከተሉት **ውስጥ አንዱን ያስሞሏቸው:**

- የሚከፈልበት እረፍት የኦሬጎን የከባድ የጤና ሁኔታ ማረጋገጫ ቅጽ
- የኦሬጎን እና የፌደራል የቤተሰብና የህክምና እረፍት የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ማረጋገጫ/ የምስክር ወረቀት
- የቤተሰብ እና የህክምና እረፍት ሕግ (FMLA) ስለ ሰራተኛ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ማረጋገጫ/ የምስክር ወረቀት የከባድ የጤና ሁኔታ ቅጽ
    - ማስታወሻ:- የዩ.ኤስ የአሰሪና ሰራተኛ መምሪያ ይህን ቅጽ ይሰጣል። በተጨማሪም ለከባድ የጤና ሁኔታ የአሰሪዎን የFMLA ማረጋገጫ/የምስክር ወረቀት እትም መጠቀም ይችላሉ።
- በጤና እንክብካቤ አቅራቢ የተሰጠ ሰነድ
- ሌላ ሰነድ — ለተፈላጊ ሰነዶች ዝርዝር የሰራተኛ መመሪያውን ይመልከቱ።

ሰነድዎ የሚከተለውን መረጃ መያዝ አለበት:

- የመጀመሪያናየመጨረሻስምዎ
- የትውልድቀንዎ

- ከባድ የጤና ሁኔታው እንደጀመረ ወይም የእረፍት ፍላጎት እንደፈጠረ የሚገመትበት ቀን
- ሁኔታው የሚቆይበት ወይም የማገገሚያ ጊዜዎ አሳማኝ ግምት
- የተቆራረጠ እረፍት ድግግሞሽና የቆይታ ጊዜ አሳማኝ ግምት እና ተግባራዊ ከተደረገ የተገመተ የህክምና የጊዜ ሰሌዳ
- ከባድ የጤና ሁኔታ ያለብዎ መሆኑን የሚገልጽ የምርመራ ወይም ሌላ መረጃ

**በFrances Online በኩል ለጥቅማ ጥቅሞች እንዴት እንደሚያመለክቱ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ለጥቅማ ጥቅሞች እንዴት እንደሚያመለክቱ የዋና ዋና ሀሳቦች ቪዲዮን በ paidleave.oregon.gov ይመልከቱ።**

ለጥቅማ ጥቅሞች ስለማመልከት በተመለከተ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የእኛን የሰራተኛ መመሪያ፣ የራሳቸውን ስራ የሚሰሩ ሰዎች መመሪያያንብቡ፣ ዉም paidleave.oregon.govን ይጎብኙ።